# 2026–2027

# የትምህርት ቤት ምደባ ለውጥ (COSA)

## የመረጃ መጽሔት

እባክዎን COSA ጥያቄዎች በሙሉ Synergy ParentVue log-inበኩል መቅረብ እንዳለባቸው ያስታውሱ።

### መግለጫ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ተማሪዎች በተመደበላቸው የመኖሪያ አካባቢ ት/ቤት ወይም ባለባቸው ግላዊ ሁኔታ ምክንያት በተመደቡበት የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ይጠበቃል። ለማጽደቅ ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ሁኔታዎች፡- በመማሪያ ክፍል ውስጥ ምን ያህል ቦታ መኖሩን፣ በክፍል ደረጃ የተመዘገቡትን ብዛት፣ የተመደቡ የሰራተኞች ብዛት፣ ወይም ትምህርት ቤቱን የሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮችን ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ይሆናል። ተማሪዎች ከአካባቢ ት/ቤት ወይም በግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ምክንያት በሚከተሉት መስፈርቶች መሠረት ከተመደቡበት ወደ ሌላ ት/ቤት ለመቀየር (COSA) ማመልከት ይችላሉ፡-

- ልዩ ችግር–ያጋጠማቸው ተማሪዎች ከአካላዊ፣ ከአእምሮአዊ፣ ወይም ስሜታዊ ደህንነታቸውን የሚነካ ወይም ከቤተሰባቸው በግል ሁኔታ ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች በትምህርት ቤት ምደባ ለውጥ ምክንያት ሊቃለሉ የሚችሉ ከሆነ COSA ማመልከት ይችላሉ።
- የቤተሰብ ዝውውር–ቤተሰቦቻቸው በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ የተዛወሩ እና በቀድሞ አካባቢያቸው ትምህርት ቤት ለመቀጠል የሚፈልጉ ተማሪዎች ልዩ የሆነ ችግር ባይኖርባቸውም COSA ማመልከት ይችላሉ። እንዲህ ያሉ ጥያቄዎች ለወቅቱ የትምህርት ዘመን ቀሪ ጊዜ ብቻ ሊቀርቡ ይችላሉ፤ ከዚህ በተለይ በ 11ኛ ወይም 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው እስከሚመረቁ እንዲቆዩ COSA ይሰጣቸዋል።
- እህት/ወንድም– ተማሪ መመዝገብ በሚፈልግበት አመት ወንድም/እህት በመደበኛው የት/ቤት ምደባ ወይም በልዩ ትምህርት ፕሮግራም የሚመዘገብበት ትምህርት ቤት ከሆነ።
  - » ወንድም ወይም እህት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የማግኔት፣ የቋንቋ ኢመርዥን የሚማሩ ከሆነ ወይም ሌላ በማመልከት ላይ የሚገኙ ወንድሞችና እህቶችን እንደየጉዳዩ ሁኔታ COSA በቋሚነት ወደሚሰጠው የትምህርት ቤት ፕሮግራም እንዲገቡ ሊፈቀድላቸው ይችላል።

COSA የተቀበሉ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ትራንስፖርት ማቅረብ አለባቸው።
የት/ቤት ማካለል ለውጥ ከተፈጠረ፣ ወይም ወንድም/እህት በቅድመ-መዋእለ ህጻናት (PreK) ውስጥ ከሆኑ ከላይ የተጠቀሱት መመዘኛዎች አይተገበሩም።

ለሁሉም የ COSA ጥያቄዎች፣ የተጠየቀው ትምህርት ቤት አዲስ ተማሪዎችን ለመቀበል ያለውን አቅም እና ሌሎች ተፅእኖ የሚፈጥሩ ጉዳዮችን ትኩረት ይሰጣል።

እነዚህ ተማሪዎች በራሳቸው ኮንሰርትየም/ክልል ውስጥ ሌላ ት/ቤት ለመግባት ሲፈልጉ COSA ጥያቄ ማቅረብ የለባቸውም፡-

- በኖርዝኢስት ኮንሰርትየም/ክልል (NEC) ወይም ዳወንካውንቲ ክልል (DCC) የሚኖሩ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በሌላ ክልል ት/ቤት የሚጠይቁ ከሆነ።
- በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማግኔት ኮንሰርሽየም (MSMC) ክልል የሚኖሩ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ወደ ሌላ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ማግኔት ኮንሰርሽየም "MSMC" ለመግባት የሚጠይቁ ከሆነ ወይም MSMC የምልመላ ሂደት ላይ በእጣ የተሳተፉ እና MSMC ትምህርት ቤት የሚያመለክቱ ተማሪዎች።
- በኮንሰርቲየም ውስጥ ባለ ሌላ ትምህርት ቤት ለመማር የሚፈልጉ ወንድሞችና እህቶች (DCC፣ NEC፣ ወይም MSMC) የተፈረመበት የጽሑፍ ይግባኝ ደብዳቤ ወደ፡- Division of Consortia Choice and Application Program Services (DCCAPS), via e-mail at DCCAPS@mcpsmd.org, located at 11721 Kemp Mill Road, Silver Spring, Maryland 20902 በኢሜይል ማቅረብ አለባቸው። NEC፣ DCC ወይም MSMC ውስጥ ያሉ ትምህርት ቤቶችን ስለመቀየር መረጃ ለማግኘት ወደ DCCAPS በስልክ ቁጥር 240-740-7800 ያነጋግሩ ወይም ይህን ድረ ገጽ ይጎብኙ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/departments/schoolchoice

እባክዎ ያስታዉሱ፡- በድንገተኛ ክስተት ምክንያት ወይም በቅርቡ ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የተዛወሩ ካልሆነ በስተቀር፣ COSA ጥያቄዎች በሙሉ እስከ ኤፕሪል 7, 2026 ድረስ መቅረብ አለባቸው።

የተማሪዎች ድጋፍ እና የትምህርት ክትትል አገልግሎት ክፍል
DEPARTMENT OF STUDENT SUPPORT AND ATTENDANCE SERVICES (DSSAS)
240-740-5620 • COSArequest@mcpsmd.org
Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL

## ዕሴት፡-

ትምህርት
መከባበር
መልካም ግንኙነት
ልህቀት/ምጡቅነት
ፍትኃዊነት

## ራእይ፡-

የወደፊት ዝግጁነት፡-
በተለዋዋጭ አለም ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች ለእድገት፣ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለመድረስ፣ እና ለስኬታማነት ዝግጁ ሆነው ይመረቃሉ— በማህበረሰባቸው ውስጥ እና ከዚያም በላይ ለመሪነት፣ ለአገልግሎት፣ እና በጎ ተጽእኖ ለመፍጠር በሚያስችላቸው እውቀት፣ ችሎታ፣ እና በራስ በመተማመን ተገንብተው ይመረቃሉ።

## ተልእኮ፡-

እምቅ አቅምን በተግባር እንዲገለጥ ማድረግ፥
ሁሉም ተማሪዎች ጥልቅ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ፣ ትምህርትን የማዳበር እና የማበልጸግ እድሎችን በመጠቀም ጠንካራ የአካዳሚክ መሠረት ይኖራቸዋል።
ሁሉም ተማሪዎች ለውጦችን እና አዳዲስ ሁኔታዎችን መቋቋም የሚችሉ ሆነው ዕድሜ ልክ የመማር ፍላጎትና ጽናትን ያዳብራሉ።
ሁሉም ተማሪዎች ትርጉም ባለው ግንኙነት ላይ የተመሠረተ መስተጋብር፤ ውጤት ላይ የሚያተኩሩ እና በትብብር የሚሠሩ ይሆናሉ። ሁሉም ተማሪዎች በማህበረሰባቸው ውስጥ አዎንታዊ ተጽእኖ ለመፍጠር የተዘጋጁ፤ እና በግል ህይወታቸው እና በሙያዊ ብቃታቸው ለስኬታማነት የሚተጉ ይሆናሉ።


**የትምህርት ቦርድ**
Board of Education

ሚ/ስ ግሬስ ሪቬራ-ኦቨን Ms. Grace Rivera-Oven
ፕሬዚደንት President

ሚ/ስ ብረንዳ ዎልፍ Ms. Brenda Wolff
ም/ፕሬዚደንት Vice President

ሚ/ስ ሪታ ሞንቶያ Ms. Rita Montoya

ሚ/ስ ካርላ ሲልቨስትሪ Ms. Karla Silvestre

ወ/ሮ ላውራ ስቲዋርት Mrs. Laura Stewart

ሚ/ስ ጁሊ ያንግ Ms. Julie Yang

ሚ/ስ ናታሊ ዚመርማን Ms. Natalie Zimmerman

ሚ/ስ አኑቫ ማሎ Ms. Anuva Maloo
ተማሪ አባል Student Member

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**
Montgomery County Public Schools

ቶማስ W. ቴይለር (ዶ/ር)
የት/ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት
Thomas W. Taylor, Ed.D., M.B.A.
Superintendent of Schools



15 West Gude Drive
Rockville, Maryland 20850
www.montgomeryschoolsmd.org

# በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

### ት/ቤት ለመቀየር እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

የትምህርት ቤት ምደባ ለውጥ (COSA) ጥያቄዎች ሁሉ መቅረብ ያለባቸው ParentVue in Synergy ParentVue Log-in ላይ ነው። አድራሻዎ አሁን Synergy ውስጥ ካለው አድራሻ የተለየ ከሆነ፣ COSA ጥያቄ ሂደት ከመከናወኑ በፊት የአሁኑ የልጅዎ ምደባ ትምህርት ቤት አድራሻውን እንዲያዘምን ማድረግ አለብዎት። COSA ጥያቄዎ ሲደርሰን አሁን የተመደበ(ች)በት ት/ቤት እና የተጠየቀው ትምህርት ቤት እንዲያውቁት ይደረጋል።

ለት/ቤት ስርአት አዲስ የሆኑ ተማሪዎች COSA ጥያቄ ከማቅረባቸው በፊት በአካባቢያቸው ት/ቤት መመዝገብ አለባቸው። COSA ጥያቄዎች ተማሪው/ዋ የመኖርያ ማረጋገጫ እና የምዝገባ ሂደት በአካባቢ ት/ቤት እስኪ(ክት)ፈፅም ድረስ አይታዩም/አይገመገሙም።

### ማመልከት ያለብኝ መቼ ነው?

ለ 2026-2027 የትምህርት አመት COSA ማመልከቻ ፌብሩዋሪ 2026 የመጀመሪያው የትምህርት ቀን እና ኤፕሪል 2026 የመጀመሪያው የትምህርት ቀን መካከል መቅረብ አለበት። ስለቀረቡት COSA ጥያቄ እስከ ሜይ 22/2026 ድረስ ለወላጆች/ሞግዚቶች እና ለተማሪዎች ውሳኔውን ለማሳወቅ የተቻለንን ጥረት እናደርጋለን። ከኤፕሪል ወር የመጀመሪያ የትምህርት ቀን በኋላ የሚቀርቡ የ COSA ጥያቄዎች ተቀባይነት የሚኖራቸው ተማሪው(ዋ) የሞንትጎመሪ ካውንቲ አዲስ ነዋሪ ከሆነ(ች) ወይም ከኤፕሪል በፊት ያልተገመተ ድንገተኛ ክስተት ካለ ብቻ ነው። ይህን ሁኔታ የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ መቅረብ አለበት። ሰነዱ ከአፕሪል ማብቂያ ቀን በኋላ የተከናወነውን የቤተሰብ እንቅስቃሴ ወይም ጉልህ የሆነ ከትምህርት ቤት ወይም ከማህበረሰብ ጋር የተያያዘ ክስተትን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት። COSA አመልክተው ዉሳኔ በመጠበቅ ላይ ያሉ/የሚጠባበቁ ተማሪዎች የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በተመደቡበት ት/ቤት መከታተል አለባቸው።

### COSA ሳመለክት በአባሪነት ማቅረብ ያለብኝ ማስረጃዎች ምንድናቸው?

በእርስዎ ግላዊ ሁኔታ ይወሰናል፣ ነገር ግን፣ ሰነዶች በተናጥል ሊረጋገጡ የሚችሉ እውነታዎችን መያዝ አለባቸው።  ለምሳሌ፡- የፋይናንስ ማስረጃዎችን፣ ከጤና ባለሙያዎች የተጻፉ ደብዳቤዎች፣ እና ከአሠሪዎች/ቀጣሪዎች የሚጻፉ ደብዳቤችን ያካትታል። እንደዚህ ዓይነት ሰነዶች በሌሉበት ሁኔታ፣ እንደዚህ ያሉ የተጋነኑ/አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የሚያሳይ ማስረጃ ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር በመመካከር ማግኘት ይቻላል።

### ልዩ ችግር ማለት ምንድን ነው?

ልዩ ችግር በቤተሰብ ግላዊ እና ግለሰባዊ ሁኔታ ላይ የሚመሰረት ነው። በአብዛኛዎቹ ቤተሰቦች ዘንድ የጋራ የሆኑ ችግሮች ለምሳሌ፡- የህፃናት መዋያ/ዴይኬር፣ ወይም የፕሮግራም/የኮርስ ምርጫ፣ የመጓጓዣ ጉዳዮች ሌሎች አሳማኝ ምክንያቶች ከሌሉ በስተቀር እንደ ከባድ ችግር-እንግልት ተደርገው አይቆጠሩም። ሁሉም የችግር ጥያቄዎች በተናጠል ሊረጋገጥ የሚችል ስነዳ ኣባሪ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፣ ኣለዚያ ጥያቄው ውድቅ ይደረጋል። እንደዚህ ዓይነት ሰነዶች በሌሉበት ሁኔታ፣ እንደዚህ ያሉ የተጋነኑ/አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የሚያሳይ ማስረጃ ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር በመመካከር ማግኘት ይቻላል። እንደዚህ ያሉ የልዩ ችግር ምሳሌዎች፣ በዚህ የሚወሰኑ ባይሆንም የሚከተሉትን ያካትታል፡-

1. የህፃናት እንክብካቤ: ወላጆች/አሳዳጊዎች እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ሠዓት በፊት እና/ወይም ከትምህርት በኋላ ከዕድሜ ጋር የሚስማማ ክትትልን ሲደረግ የማይመቻቸው ሁኔታዎች ካሉ መግለጽ አለባቸው፡- (a) የሥራ ሰዓታቸው በቤት አካባቢ ለሚገኙት ት/ቤቶች የልጆች እንክብካቤ ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ከሚሰጠው ዓይነተኛ ሰዓት በላይ ወይም በቀላሉ ሊደረስባቸው የሚችሉ የሕፃናት እንክብካቤ ፕሮግራሞች ላይ በእጅጉ የሚራዘም  ይሆናል፤ እና/ወይም (b) ከፍተኛ የፋይናንስ እጥረት ደግሞ ቤተሰቡ የልጆችን እንክብካቤ በሌላ መንገድ የማግኘት ችሎታቸውን ይገድባል ወይም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የተማሪዎችን ፍላጎት ይገድባል። (c) በርካታ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቤቶቻቸው ሕንፃ ውስጥ ወይም በአቅራቢያ የሕጻናት እንክብካቤ አገልግሎት ይሰጣሉ።
   - ብዙ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቤቱ ሕንፃ ውስጥ ወይም አቅራቢያ ላይ የሕፃናት ማቆያ እንክብካቤ ይሰጣሉ።
   - ቀደም ሲል የተጠቀሙበት የሕፃናት እንክብካቤ ሰጪ ወይም ተማሪው(ዋ) ከተንከባካቢ ጋር የተለማመደ ቢሆንም ተማሪው(ዋ) ከተመደበ(ች)በት ትምህርት ቤት ክልል ውጭ ከሆነ ምርጫው እንደ ልዩ ችግር አይቆጠርም። በተጨማሪም በህፃናት እንክብካቤ ስኮላርሺፕ ፕሮግራም (CCS) እና ሰራተኛ የሆኑ ወላጆች እርዳታ ፕሮግራም (WPA) በኩል የገንዘብ ድጋፍ ይገኛል።
   - የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ያደጉ በመሆናቸው ከትምህርት ቤት ሠዓት በፊት እና በኋላ ለአጭር ጊዜ ራሳቸውን መንከባከብና መቆጣጠር ይችላሉ። ይህ ወደ ትምህርት ቤት እና ከት/ቤት ወደቤታቸው በእግር መሄድን፣ በተመደበላቸው የ MCPS ትምህርት ቤት አውቶብስ መሳፈር እና ከደረሱ በኋላ መውረድ፣ እንዲሁም ወላጆች/አሳዳጊዎች ከስራ ወደ ቤት እስከሚመለሱ ድረስ ተማሪዎቹ ክትትል ሳይደረግባቸው በቤታቸው ውስጥ መቆየትን ሊያካትት ይችላል ነገር ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም። በተጨማሪም፤ ብዙ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከት/ቤት ሠዓት በኋላ እስከ ምሽት ድረስ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ይሰጣሉ።
2. የተማሪን አካላዊ፣ አእምሯዊ ወይም ስሜታዊ ደህንነትን በሚመለከት የማቅለል ሁኔታዎች። በዚህ ምክንያት COSA  የሚጠይቁ ወላጆች/አሳዳጊዎች የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ አለባቸው ፡- (a) በቀጥታ ከትምህርት ቤቱ አካባቢ ጋር የተያያዙ ወይም በከፍተኛ ሁኔታ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የተማሪን አካላዊ፣ አእምሯዊ ወይም ስሜታዊ ደህንነት በተመለከተ በጤና አጠባበቅ ባለሙያ የሚሰጠው ቀጣይ ሕክምና፤ እና/ወይም (b) ልዩ የእንክብካቤ መስፈርቶች ያሉት ጉልህ የጤና ጉዳዮች።

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ተማሪዎች የመኖሪያ አካባቢያቸውን መሠረት በማድረግ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በሚመደቡበት ትምህርት ቤት እንዲማሩ ይጠበቅባቸዋል። የትምህርት ቤት ምደባ የሚከናወነው MCPS የትምህርት ቤት ድልድል መመሪያን በመጠቀም ነው። የትምህርት ቤት ብሔራዊ የደረጃ/እርከን፣የትምህርት አቅርቦት፣ የኢንተርስኮላስቲክ አትሌቲክስ ሪከርዶች፣የተማሪ ምዝገባ እና አቅም ግንባታ፣ስለ ደህንነት መላምት፣ ከትምህርት የመታገድ

ሁኔታ፣ ወይም የተማሪ በትምህርት ላይ የመገኘት መጠን እንደ ልዩ ችግር አይቆጠርም።

ቀደም ሲል በዚያ ትምህርት ቤት የመከታተል ወይም የልዩ ችግር በቅድመ ትምህርት ቤት ፕሮግራም ውስጥ ለመቆየት እንደ ቅድመ ሁኔታ አይጠየቅም።

### ለልጄ COSA አንዴ ከተፈቀደለ(ላ)ት፣ በየአመቱ ማመልከት ያስፈልገኛል?

COSA የተፈቀደለ(ላ)ት ለአንድ አመት ብቻ ካልሆነ በስተቀር ተማሪው(ዋ) ወደሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ (ማለትም - መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) እስከሚዛወር/እስከምትዛወር ድረስ COSA በተፈቀደለ(ላ)ት ትምህርት ቤት መቆየት ይችላል/ትችላለች። በአካባቢያቸው ት/ቤት COSA የተፈቀደላቸው ተማሪዎች ከአንደኛ ደረጃ ወደ መካከለኛ ደረጃ፣ እና ከመካከለኛ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሸጋገሩ COSA እንዲፈቀድላቸው እንደገና ማመልከት እና ልዩ የሆነ ምክንያት ማቅረብ አለባቸው።

### ልጄ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የማይሰጥ የልዩ ትምህርት አገልግሎት እየተከታተለ(ች) ቢሆንስ?

የተማሪዎ ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) በሁሉም ትምህርት ቤቶች የማይሰጡ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን የሚፈልገው/የሚያስፈልጋት ከሆነ፣ተማሪው(ዋ) የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን እንደሚያገኝ/እንደምታገኝ በመግለጽ COSA ያስፈለገበትን ምክንያት ጭምር ParentVue COSA ማመልከቻ ሞልተው ከተገቢ ሰነዶች ጋር አያይዘው ማቅረብ አለብዎት ። በሁሉም ት/ቤቶች የማይገኙ ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች በመቀበል ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች የሚደረጉ ጥያቄዎችን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ከጁላይ 1 በኋላ ይደረጋሉ። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን የልዩ ትምህርት አገልግሎት መምሪያን በስልክ ቁጥር 240-740-3900 ያነጋግሩ።

### የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሥራ ባልደረቦች ተማሪዎቻቸው በቀጥታ COSA ይፈቀድላቸዋል?

በቀጥታ አይፈቀድምነገር ግን Title I ትምህርት ቤቶች ወይም ትኩረት ትምህርት ቤቶች/Focus Schools ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞችን ለማበረታታት እና ለመደገፍ ከ MCPS ስልታዊ ትኩረት አንጻር፣ በነዚያ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚሠሩ ሰራተኞች በሚከተሉት ሁኔታዎች መሠረት በሚሰሩበት ትምህርት ቤት ለልጆቻቸው ዝውውር መጠየቅ ይችላሉ።

a. ለመጪው የትምህርት ዓመት ከዚህ በላይ በተገለጹት ትምህርት ቤቶች በሙሉ ጊዜ ሠራተኛነት (FTE) የተመደበ(ች) እና የዓመት ፈቃድ፣ የጡረታ፣ እና የጤና ሽፋን ጥቅማጥቅሞች ያለው በጀት ተመድቦለ(ላ)ት የሚሠራ-የምትሠራ ሠራተኛ፥ እና

b. የሥራ ባልደረባው(ዋ) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ የሆነ(ች) እና ተማሪው(ዋ) ወደ MCPS ለመመዝገብ ብቁ የሚሆን-የምትሆን ከሆነ(ች)፣ እና

c. ጥያቄው በሠራተኛው(ዋ) የሥራ ቀን ውስጥ በሁሉም ጊዜያት የልጆች እንክብካቤ እቅድ አስፈላጊ ከሆነ አብሮ ይመጣል።

ሰራተኛዉ(ዋ) በሚሠራበት/በምትሰራበት ትምህርት ቤት የተማሪው(ዋ) መመደብ ሰራተኛው(ዋ)ን ስራዉን(ዋ)ን አጥጋቢ በሆነ መንገድ የማከናወን ችሎታዉ(ዋ)ን የሚያደናቅፍ ከሆነ፣ የተማሪ ዝውውሩ እንደገና ሊታገድ ይችላል።

በዚህ ክፍል ከተገለፁት ትምህርት ቤቶች በአንዱ የማይሰሩ የ MCPS ሰራተኞች በዚህ ፖሊሲ እና ተዛማጅ ህጎች መስፈርቶች መሰረት ለልጆቻቸው COSAs ማመልከት ይችላሉ።

### የዝውውር ሂደቱ ለጥንድ የአንደኛ ደረጃ/ኤሌሜንተሪ ት/ቤቶችም ተመሳሳይ ነው ወይ?

አዎን። አንድ ተማሪ በተፈቀደ COSA አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ቤል ፕሬ፣ ሞንትጎመሪ ኖልስ፣ ኒው ሃምፕሻየር ኢስቴትስ፣ ሮስኮ አ. ኒክስ፣ ሮዝሜሪ ሂልስ እና ታኮማ ፓርክ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች) ጣምራ የሚማር/የምትማር ከሆነ(ች) ከፍ ወዳለ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት COSA እንዲፀድቅላቸው ጥያቄ ማቅረብ አለባቸው።

### ወደ ፑልስቪል ኤለመንተሪ ት/ቤት የተመደቡ እና ሞነከሲ ኤለመንተሪ ት/ቤት ለመከታተል የሚፈልጉ ተማሪዎች አካሄዱ እንዴት ነው?

ወላጆች/አሳዳጊዎች COSA ማመልከቻ ማቅረብ ያለባቸው ParentVue ላይ ሲሆን በዚህ አይነት በፍጥነት ሊፀድቅ ይችላል።

### COSA ለአካዳሚክ ሲግኔቸር ፕሮግራሞች ወይም ለተለዩ ኮርሶች ይፈቀዳል?

አይፈቀድም፡- ሲግኔቸር ፕሮግራሞች እና ልዩ ኮርሶች የተዘጋጁት ለሚገኙበት ትምህርት ቤት ነው። ወደነዚህ ት/ቤቶች የሚቀርቡ COSA ጥያቄዎች ከሁሉም ሌሎች COSA ጥያቄዎች ጋር ተመሳሳይ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው። COSA ስለማይመለከታቸው ፕሮግራሞች በዚህ ቡክሌት ገጽ 5 ይመልከቱ

### ተማሪዎች ለአካደሚያዊ ዝውውር COSA ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ?

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ከሚከተሉት በአንዱ ለመሳተፍ አካደሚያዊ ዝውውር ጥያቄ ለማቅረብ ይችላሉ፡-

1. በዲስትሪክቱ ወይም በትምህርት ቤት የኮርስ ካታሎግ ዝርዝር ውስጥ እንደተገለጸው በተማሪው(ዋ) የአካባቢ ት/ቤት ውስጥ የማይገኙ ተዛማጅ የሆኑ በተከታታይ ብዙ ዓመት ለሚወሰዱ ኮርሶች። ይህ የሚያመለክተው በተማሪው የአካባቢ ትምህርት ቤት የማይሰጥ እና በዋና ኮርስ እና/ወይም በፕሮግራም ማጠናቀቂያ የሚያበቃ ከሙያ ጋር በተያያዙ የትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ CTE (የሙያ እና የቴክኒክ ትምህርት) ውስጥ ያሉ ተዛማጅ ኮርሶችን ነው።
2. በተማሪው(ዋ) አካባቢ ትምህርት ቤት የማይገኝ ፣ በዲስትሪክቱ ወይም በት/ቤት የኮርስ ማውጫ ውስጥ እንደተገለፀው የበርካታ ዓመታት ተከታታይነት ያለዉ ነጠላ ኮርስ። ይህ በተማሪው(ዋ) የአካባቢ ትምህርት ቤት ውስጥ የማይሰጥ ልዩ ትምህርት የላቀ ደረጃ ጥናትን የሚያስከትል የብዙ-ዓመት ኮርስ ቅደም ተከተልን ይመለከታል።

ምሳሌዎች፡-

አረብኛ 1፣ አረብኛ 2፣ አረብኛ 3

ታፕ ዳንስ/ዳንኪራ 1፣ ታፕ ዳንስ/ዳንኪራ 2፣ ታፕ ዳንስ/ዳንኪራ 3

ማሳሰቢያ፡- በመጀመሪያው የት/ቤት ቀን መቅረብ አለበትፌብሩወሪ 2026እና የመጀመሪያው የት/ቤት ቀን ኤፕሪል 2026። አመልካቾች ቦታ ካለ ይፈቀድላቸዋል። የእህትማማች/ወንድማማች ግንኙነት አይሠራም። ተማሪ ከፕሮግራሙ ለመውጣት ከወሰነ(ች) ወደ አካባቢ ትምህርት ቤት ይመለሳል/ትመለሳለች። የተፈቀደላቸው ተማሪዎች ለ MCPS የተማሪ ዝውውር ፖሊሲ ተገዢ ይሆናሉ። (https://ww2.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/jee.pdf).

COSA መስፈርቶች ነፃ የሆኑ ፕሮግራሞች ይኖራሉ?

የሚከተሉት ፕሮግራሞች የዝውውሩ አካል ያልሆኑ በማመልከቻ ሒደት ተደራሽነት ያላቸው ምሳሌዎች ናቸው። ነገር ግን፣ ሌላ የምልመላ መስፈርት ሊተገበር ይችላል።

- በኮ/ሎ ዛዶክ መግሩደር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የአቪዬሽን እና ኤሮስፔስ
- በሞንትጎመሪ ብሌር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የኮሙኒኬሽን አርትስ ፕሮግራም
- በጆን ኤፍ. ኬኔዲ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሪጅናል ኢንተርናሽናል ባከልዮሬት ዲፕሎማ ፕሮግራም
- በስፕሪንግብሩክ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሪጅናል ኢንተርናሽናል ባከልዮሬት ዲፕሎማ ፕሮግራም
- በዋትኪንስ ሚል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሪጅናል ኢንተርናሽናል ባከልዮሬት ዲፕሎማ ፕሮግራም
- በሪቻርድ ሞንትጎመሪ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ካውንቲ አቀፍ ሪጅናል ኢንተርናሽናል ባከልዮሬት ዲፕሎማ ፕሮግራም
- በኬኔዲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአመራር ማሰልጠኛ ተቋም
- ሳይንስ፣ ሒሳብ፣ ኮምፒውተር ሳይንስ ፕሮግራም በሞንትጎመሪ ብሌር ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
- በዊተን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት PLTW የምህንድስና ፕሮግራም
- በዊተን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት PLTW ባዮሜዲካል ፕሮግራም
- ቪዥዋል አርት ማእከል በአልበርት ኢንስታይን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Visual Art Center at Albert Einstein High School)
- የጤና እንክብካቤ ሙያ በ ባዮሳይንስ አካደሚ በዊተን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና በ ቶማስ ኤዲሰን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Healthcare Professions - Biosciences Academy at Wheaton High School and Thomas Edison High School of Technology)
- የመስተንግዶ እና ቱሪዝም ማኔጅመንት በግሎባል ስተዲስ አካደሚ በዊተን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና በ ቶማስ ኢድሰን ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የቴክኖሎጂ ት/ቤት (Hospitality and Tourism Management - Global Studies Academy at Wheaton High School and Thomas Edison High School of Technology)
- ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ሳይበር ሰኩሪቲ-አካደሚ ኦቭ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በዊተን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና በ ቶማስ ኢድሰን የቴክኖሎጂ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
- የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት እና ምህንድስና አካደሚ ኦቭ ኢንጅነሪንግ በዊተን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና በቶማስ ኤዲሰን የቴክኖሎጂ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
- መካከለኛ ደረጃ ኮሌጅ በኖርዝውድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሞንትጎመሪ ኮሌጅ MC2 ፕሮግራም
- በሮክቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት PLTW ባዮሜዲካል ሳይንስ IB ሙያዊ ፕሮግራሞች
- በሮክቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት PLTW ኢንጅነሪንግ IB ሙያዊ ፕሮግራሞች
- የመስተንግዶ ማኔጅመንት IB ሙያዊ ፕሮግራሞች በሮክቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
- በሮክቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት -ኮምፒውተር ሳይንስ IB ሙያ ፕሮግራሞች
- በሮክቪል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቻይልድ ደቨሎፕመንት አሶሽዬት IB የሙያ ፕሮግራሞች
- በፑልስቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ግሎባል ኢኮሎጂ
- ሳይንስ፣ ሒሳብ፣ ኮምፒውተር ሳይንስ ፕሮግራም በፑልስቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
- በፑልስቪል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ስለ ሰብአዊነት (ሑማኒቲስ)
- በሴኔካ ቫሊ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የጤና ጥበቃ ሙያ
- በሴኔካ ቫሊ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መስተንግዶ እና ቱሪዝም ማኔጅመንት
- ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ሳይበር ሰኩሪቲ በ ሴኔካ ቫሊ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
- በሴኔካ ቫሊ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት እና አርኪቴክቸር
- በሴኔካ ቫሊ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮጀክት ሊድ ዘ ዌይ ኢንጅነሪንግ
- በኖርዝዌስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሞንትጎመሪ ኮሌጅ መካከለኛ ደረጃ ኮሌጅ (MC2) ፕሮግራም
- በጌትስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት PLTW ባዮሜዲካል ሳይንስ
- በክላርክስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኔትዎርክ ኦፐሬሽንስ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (PTECH)
- በዊትማን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለ ማህበራዊ ፍትህ አመራር
- በሼርዉድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የግብርና ሳይንስ ሥርዓተ ትምህርት
- በኢስተርን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁንየር መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁማኒቲስ እና ኮሙኒኬሽን ማግኔት ፕሮግራም።
- በታኮማ ፓርክ ሚድል ስኩል እና ሮቤርቶ ክለመንቴ ሚድል ስኩል ሳይንስ፣ ሒሳብ፣ እና ኮምፒውተር ሳይንስ ማግኔት ፕሮግራም
- የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ማግኔት ኮንሰርሽዩም (አርጋይለ፣ ሎኢ.ደርማን፣ ፓርክላንድ)
- ጠንካራ የዳበረ ትምህርት ጥናት ማእከሎች
- በማንኛውም የኤሌሜንታሪ ወይም መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የቋንቋ ኢመርዥን ፕሮግራም የተመደቡ ተማሪዎች
- በት/ቤቶች ሱፐርኢንተደንት የሚለዩ ሌሎች ፕሮግራሞች
- በአማራጮች (OPTIONS) ላይ እንደተገለጸው ሌሎች ፕሮግራሞች፡- የካውንቲ አቀፍ ፕሮግራሞች መመሪያ (www.montgomeryschoolsmd.org/departments/enrichedinnovative/options)

ለአካዳሚክ ዝውውር COSA የተፈቀደላቸው ተማሪዎች ከፕሮግራሙ ከወጡ ወደ አካባቢያቸው ትምህርት ቤት መመለስ ይጠበቅባቸዋል፡-

(ይህን ድረገጽ ይመልከቱ፡- ww2.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/pdf/jee.pdf)

### COSA ጥያቄዬን ካቀረብኩ በኋላ ምን ሊሆን ይችላል?

ያቀረቡት COSA ጥያቄ ወደ DPPAS የሚተላለፍ ሲሆን፤ DPPAS በየዓመቱ 3,000 እስከ 4,000 ጥያቄዎችን ይቀበላል። ውሳኔ ከመስጠቱ አስቀድሞ DPPAS መጣራት ያለባቸውን ነገሮች ያጠናቅቃል። የአካዳሚክ ዝውውር/ለውጥ የማድረግ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ፣ የፕሮግራም ጥያቄውን መተንተን እና ከቤተሰብ ጋር መገናኘት እንዲቻል COSA ወደ "Office of Teaching, Learning, and School" ይተላለፋል።

### ጥያቄዬ መጽደቁን ወይም ውድቅ መደረጉን መቼ ነው የምሰማው?

DSSAS ሰራተኞች ሜይ 22, 2026 በፊት ParentVue ላይ ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች እና ለተማሪዎች ለማሳወቅ የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ።

### ልጄ COSA ከተፈቀደለ(ላ)ት በኋላ እንደገና ውድቅ ሊደረግ ይችላል?

አንድ ርእሰመምህር COSA በተገቢው ምክንያት እንዲሰረዝ ሊጠይቅ ይችላል። ለምሳሌ፥ የዲሲፕሊን ጥሰት ወይም በትምህርት ላይ ያለመገኘት ጉዳይ ሊሆን ይችላል።

### በአዲሱ ት/ቤት ልጄ በት/ቤቶች የስፖርት ውድድር ለመጫወት ብቃት ይኖረዋል/ራታል?

በወቅቱ ከራሳቸዉ የመጋቢ ት/ቤት ዉጪ COSA የሚያገኙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አትሌቲክስ እንዲቀርላቸው ካላመለከቱ በስተቀር፣ በአትሌቲክስ ከመሣተፋቸው አስቀድሞ ለአንድ የካለንደር ዓመት በአዲሱ ት/ቤት መከታተል አለባቸው። እባክዎ ለበለጠ መረጃ የአትሌቲክስ ዲፓርትመንትን ድረ ገጽ ይመልከቱ።

### ወደ አዲሱ ት/ቤት ትራንስፖርት ይቀርባል ወይ?


አይደለም። የመጓጓዣ አገልግሎት መስጠት የወላጅ/የሞግዚት ኃላፊነት ነው።

### የኔ COSA ጥያቄ ተቀባይነት ካላገኘ ሁኔታዎቹን እንደገና እንዲያጤኑ መጠየቅ የምችለው እንዴት ነው?

ስለ COSA የተሰጠው ውሳኔ አግባብ አለመሆኑን ካመኑበት ለሱፐርኢንተንደንቱ/ተወካይ በዚህ ኢሜል አድራሻ ማመልከት ይችላሉ፦-DivisionOfAppeals@mcpsmd.org ይግባኙ ውሳኔው ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ ለሱፐርኢንተንደንቱ/ተወካይ በጽሁፍ መቅረብ አለበት። ይግባኙ ውሳኔው እንዲቀለበስ የሚፈያስፈልግበትን ምክንያት(ቶች) እና በተጨማሪ እንዲታይልዎት የሚፈልጉትን ማንኛውንም ተጨማሪ መረጃ ማካተት አለበት። ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 240-740-4130 ይደውሉ። COSA ይግባኝ ላይ ውሳኔ የሚጠባበቁ ተማሪዎች የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በተመደቡበት ት/ቤት ይከታተላሉ።

ይግባኝ በሙሉ የሚታየው በቀረቡት ሠነዶች እና በክትትል ኮሚዩኒኬሽን/ግንኙነት ላይ ተመስርቶ ነው።

ለሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ያቀረቡት ይግባኝ ውድቅ ከተደረገ የሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ውሳኔ ደብዳቤ በደረሰዎት 30 ቀናት ውስጥ ለሞንትጎምሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ (ቦርድ)፣ በዚህ የኢሜል አድራሻ boeappeals@mcpsmd.orgይግባኝዎን በተቻለ ፍጥነት እንዲያቀርቡ እናበረታታለን። ሁሉም ይግባኞች የሚሰሙት በቦርዱ መደበኛ የስብሰባ ቀኖች ነው። ቦርዱ በኦገስት ወር እረፍት ላይ እንደሚሆን እባክዎ ያስታውሱ።




ParentView ለመክፈት
ይህን QR ኮድ ስካን ያድርጉ

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፦ "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል" ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

በሜሪላንድ ስቴት የሚገኙ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የህዝብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ት/ቤቶች በሙሉ የሚከተሉትን ህጎች በማክበር እንዲሠሩ የስቴቱ ፖሊሲ/ድንጋጌ ነው፦

(1)የፌደራል ታይትል VI የዜኘት መብቶች ደንብ 1964፣ እና

(2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፦

- (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
- (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
- (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

የግንኙነት መርጃዎች እና የፌደራል፣ የስቴት፣ ወይ የአካባቢ መስፈርቶች በተለያዩ ሕትመቶች መካከል ልዩነት ሊኖራቸው ስለሚችል በዚህኛው ህትመት ላይ የተካተተው የሚፀና መሆኑን ልብ ይበሉ። ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት እባክዎን ይህን በይነመረብ ይመልከቱ፦ www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination.

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | MCPS ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ *** |
|---|---|
| Director of Student Conduct and Appeals<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator ሰክሽን 504 አስተባባሪ<br>Division of Specialized Support Services, Department of School Counseling<br>850 Hungerford Drive, Room 170, Rockville, MD 20850<br>240-987-8031 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | |
| Title IX Coordinator<br>Division of Equity and Organizational Development, Department of Student Conduct and Appeals<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ ማሳወቂያ የተሻሻለውን የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።

**ይህ ማሳወቂያ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር ይጣለጣል።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል። U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), 61 Forsyth St. S.W., Suite 19T10, Atlanta, GA 30303, 404-974-9406 and TDD: 800-877-8339, OCR.Atlanta@ed.gov, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ"Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፦ 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL
ሕትመት፦ Division of Communications for the Chief of District Operations
0702.26ggk • Editorial, Graphics & Publishing Services • 1/26 • 12,520
የቅጂ መብት፦ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ፣ ሮክቪል፣ ሜሪላንድ
Copyright © 2025 Montgomery County Public Schools, Rockville, Maryland